3ኛ ፍትሐ ብሔር ጉዳፈቻ ችሎት ባለጉዳዮች በሙሉ

- የጉዲፈቻ ውል ስምምነት እንዲፀድቅ ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ ሲቀርብ ከአቤቱታው ጋር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 መሰረት ተከታዮቹ ማስረጃዎች በአቤቱታ ዝርዝር መግለጫ ላይ በግልጽ ተጠቅሰውና ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል ::

ሀ) የጉዲፈቻ ውልን በተመለከተ

- የጉዲፈቻ ውል በኢ/ፌ/ዴ/ሪ/ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 180 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና በፍትሐ ብሔር የውል ህግ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል ::
- በውሉ ይዘት ላይ የጉዲፈቻ ሰጪዎች እና የጉዲፈቻ ተቀባዮች ሰም እስከነአያት እና ዜግነታቸውን መገለጽ አለበት ::
- የጉዲፈቻ ውሉ ይዘት ላይ የህፃኑ ሰም እና የትውልድ ዘመኑ መጠቀስ ያለበት ሲሆን የጉዲፈቻ ተደራጊው ህፃን ለጉዲፈቻ አድራጊዎች ለመሰጠት መነሻ የሆነውን ምክንያት መገለጽ ይኖርበታል ::
- የጉዲፈቻ ውሉ ላይ ተዋዋይ ወገኖች እና ቢያንስ ሁለት ምስክሮች በግልጽ ፊርማቸውን ወይም/እና ሊሚቸውን ማስቀመጥ አለባቸው ::
- የጉዲፈቻ ውሉ በ5 ሶርሺናል ሰነድ ይዘጋጃል፤ የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃን የቅርብ ፎቶ ግራፍ (ፓስፖርት ሳይዝ) ጀርባ ላይ በጉዲፈቻ ሰጪዎች ስለ ትክክለኛነቱ ከተፈረመበት በኃላ በ5ቱም ሶርሺናል ሰነድ ላይ ተያዞ/ተለጥፎ እና ተገቢው የቴምብር ቀረጥ ተከፍሎበት መቅረብ ይኖርበታል ::

Scanned by CamScanner

- የልደት ምስክር ወረቀት ወይም የሲደት ሰርተፍኬት ፣
- የህክምና ምስክር ወረቀት ወይም ሜዲካል ሰርተፍኬት ፣
- የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃን ወላጅ/ወላጆች በሕይወት ከሌሉ የሞት ምስክር ወረቀት ወይም በህይወት የሌሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፣
- የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃን ወላጅ/ወላጆች የጠፉ ከሆነ ሰለመጥፋታቸው የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ ፣
- የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃት ወላጅ አባት የማይታወቅ/ከማይታወቅ ሰው የተወለደ ከሆነ ይህንኑ በቃለመሃላ አረጋግጦ ማቅረብ ፣
- የጉዲፈቻ ተደራጊ ህፃን የህይወት ታሪክ ባጭሩ ለብቻው ተፅፎ እና በጉዲፈቻ ሰጪዎችም ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል ::

ሐ) <u>የጉዲፈቻ አድራጊዎችን በተመለከተ ሊቀርቡ የሚገባቸው ማስረጃዎች</u>

Scanned by CamScanner

- የጉዲፈቻ ተደራጊውን ህፃን በጉዲፈቻ ለመስጠት የሚያስችል መብት ያላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሞግዚትነትና የአሳዳሪነት ማስረጃ ፣
- የጉዲፈቻ ተደራጊውን ህፃን በራሳቸው የኢኮኖሚ አቅም ለማሳደግ፣ ለማስተማር፣ ለመንከባከብ እና አስፈላጊውን ነገር ለማሟላት የሚችሉ ድሃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ከሚኖሩበት <u>ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት</u> ወይም <u>ከወረዳው ሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት</u> ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ::

<u>ማሳሰቢያ</u>

- ከላይ የተገለፁት ሁሉም ማስረጃዎች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ሰድስት ወር ያላለፋቸው መሆን አለባቸው ::
- አንዳንድ የሰነድ ማስረጃዎች በውጭ ሃገር የተዘጋጁ ወይም የቀረቡ ከሆነ ሰለ ሕጋዊነታቸው በኢ/ፌ/ዴ/ሪ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ተረጋግጠው ካልቀረቡ የማናስተናግድ መሆኑን እናሳውቃለን ::
- የጉዲፈቻ ውል በውክልና ከሚፈረምም ይሁን ፍርድ ቤት ቀርቦ ለማስወሰን የሚቻለው ይህንኑ ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ልዩ ውክልና ይዞ መቅረብ ያስፈልጋል :: ልዩ ውክልና ካልቀረበ በጠቅላላ ውክልና የማናስተናግድ መሆኑን ለማሳሰብ እንወዳለን ::

Scanned by CamScanner